ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ

በዚህ የቅብብሎሽ መሰመር፦

ብፁዕ*
GARLAND F. BYERS, JR., J.D., D.D.‡
የአሕዛብ ጳጳስ፣ በሐዋርያዊ ተልእኮ



የመጨረሻው ራት፣ በሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ (1495-1498)፣ ሚላን በሚገኘው የሳንታ ማሪያ ዴሌ ግራዚዬ ገዳም የምግብ አዳራሽ ውሰጥ፦ ጌታችን ከአሥራ ሁለቱ ጋር።

የሕዝብ ንብረት።

የሐዋርያዊ ቅብብሎሽ ምንነት

ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ እያንዳንዱ ጳጳስ ከእርሱ በፊት በነበሩት እጅ መጫን የተሾመበት፣ ክርስቶስ እስከ ላካቸው ሐዋርያት ድረስ የሚዘልቅ ያልተቋረጠ የጳጳሳት መሰመር ነው። የጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷ ከሐዋርያት ራሳቸው የወረደ መሆኑን ለመመስከር ይህን ትጠቅስ ነበር፦ የሮሙ ቅዱስ ቀሌምንጦስ እ.ኤ.አ. በ96 ገደማ ሰለዚሁ ጽፏል፤ የሊዮኑ ቅዱስ ኢሬኔዎስም እ.ኤ.አ. በ180 ገደማ የሮም ጳጳሳትን ቅብብሎሽ ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ ራሱ ዘመን ድረስ ዘርዝሯል።

ክርስቲያኖች በዚህ ጉዳይ አሰፈላጊነት ላይ አይስማሙም። ብዙ ቤተ እምነቶች ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ ምንም ፋይዳ እንደሌለው፣ የቤተ ክርስቲያንም ታማኝነት የሚገኘው በየትኛውም የጳጳሳት መሰመር ሳይሆን የሐዋርያትን ትምህርት በመጠበቅ እንደሆነ ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ለእውነተኛ አገልግሎትና ለእውነተኛ ምሥጢራት አሰፈላጊ እንደሆነ ይቁጥሩታል፤ ከእነርሱም መካከል የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት፣ የምሥራቃውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ይገኙበታል፤ የአንግሊካንና አንዳንድ የሉተራን አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ እንደ ውድ ሀብት ይጠብቁታል። በብዙ ቤተ እምነቶች ውስጥም ቢሆን፣ አንድ ጳጳስ ከክርስቶስ ሐዋርያ በቅብብሎሽ መውረዱ ምን ያህል አሰፈላጊ ነው በሚለው ጉዳይ ላይ አመለካከቶች የተለያዩ ናቸው።

አሥራ ሁለቱና ሰብዓው

በክርስትና እምነት ውስጥ አንዳንዶች በመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና ጌታ «ሾመ»፣ «ሁለት ሁለትም አድርጎ ... በፊቱ ላካቸው» በተባለላቸው በሰብዓው መካከል ልዩነት ያደርጋሉ (የሉቃስ ወንጌል 10:1)። ሁለቱም የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩ፣ እንዲፈውሱና ሥልጣኑን እንዲሸከሙ በክርስቶስ ራሱ ተልእኮ ተቀብለዋል፦ «የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል» (የሉቃስ ወንጌል 10:16)።

ጳጳስ ባየርስ ሰብዓው ክርስቶስን በአካል ያውቁት እንደ ነበረና ተልእኳቸውንም ከእርሱ በአካል እንደ ተቀበሉ ያምናሉ፤ ጌታም ሥራውን እንዲሠሩ ይልካቸው ዘንድ በሚገባ ያውቃቸው ነበር። በዚህም ምክንያት ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ የመጀመሪያዎቹን አሥራ ሁለቱን ብቻ ሳይሆን ሰብዓውንም ያጠቃልላል ብለው ያምናሉ። ከትንሣኤ በኋላ የአሕዛብ ሐዋርያ ሆኖ የተጠራው ቅዱስ ጳውሎስ በአሥራ ሁለቱ ዘንድ እንደ እውነተኛ ሐዋርያ ተቀባይነት አገኘ፤ እነርሱም «ቀኝ እጃቸውን» ሰጡት (ወደ ገላትያ ሰዎች 2:9)።

በእነዚህ ገጾች ያሉት የቅብብሎሽ መሰመሮች

ጳጳስ ባየርስ ሐዋርያዊ የቅብብሎሽ መሰመሮቻቸውን ለሕዝብ ምርመራና ለክርስቲያን ምእመናን ጥቅም እዚህ ይዘረዝራሉ። እያንዳንዱ ገጽ አንድን መሰመር ከሐዋርያው ጀምሮ፣ ጳጳስ በጳጳስ፣ እስከ ጳጳስ ባየርስ ድረስ ይከታተላል። በአብዛኛው ሁኔታ እያንዳንዱ መሰመር እስከ ሐዋርያው ድረስ፣ በገጹ ላይ የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት የሚጠብቋቸውን የጳጳሳት ዝርዝሮች ራሳቸውን ይከተላል፤ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸውን ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ የሚከታተሉባቸው ያው ዝርዝሮች ናቸው፤ በእያንዳንዱ መሰመር የተጠቀሱት ቅዱሳንም እነዚሁ አብያተ ክርስቲያናት የሚያከብሯቸው ናቸው።

የጳጳስ ባየርስ የራሳቸው የሹመትና የሚመተ ጵጵስና ምስክር ወረቀቶች፣ ከሚመተ ጵጵስናቸው ፎቶግራፎች ጋር፣ በ«ስለ ጳጳሱ» ገጽ ላይ ቀርበዋል።

ስለ ሰብዓው የትኛውም አመለካከት ቢያዝ፣ ጳጳስ ባየርስ ከመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለቱ ከአራቱ፣ ማለትም ከቅዱስ ጴጥሮስ፣ ከቅዱስ እንድርያስ፣ ከቅዱስ ዮሐንስና ከቅዱስ ቶማስ፣ እንዲሁም ከአሕዛብ ሐዋርያ ከቅዱስ ጳውሎስ ትክክለኛ ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ አላቸው። በዚህ አጋጣሚ የሚከተለውን መጥቀስ ይቻላል፦ እ.ኤ.አ. በ2026 ባለው ሁኔታ፣ የአሁኑ የሮማ ጳጳስ በዋናው የሚመት መስመራቸው ሐዋርያዊ ቅብብሎሻቸውን የሚያደርሱት ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ ብቻ ነው፤ የአሁኑ የሞስኮና የመላው ሩሲያ ፓትርያርክም በዋናው የሚመት መስመራቸው ሐዋርያዊ ቅብብሎሻቸውን በተመሳሳይ በአንጾኪያ መንበር በኩል ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ ብቻ ያደርሳሉ። የአሁኗ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳሳት በዋናው የሚመት መስመራቸው ሐዋርያዊ ቅብብሎሻቸውን በካንተርበሪ መንበር በኩል ወደ አንድ ሐዋርያ ብቻ ያደርሳሉ፤ የአሁኑ የአንጾኪያ የሶርያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ በዋናው የሚመት መስመራቸው በአንጾኪያ መንበር በኩል ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ ብቻ፤ እና የአሁኑ የአሦር የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊኮስ-ፓትርያርክ በዚያች ቤተ ክርስቲያን ዝርዝር መሠረት በሰሌውቅያ-ክቴሲፎን መንበር በኩል ወደ ቅዱስ ቶማስ ያደርሳሉ።

ሰብዓውን በተመለከተ፣ ጳጳስ ባየርስ አብያተ ክርስቲያናት ከሰብዓው ሐዋርያት መካከል ከሚያከብሯቸው ከአምስቱ ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ አላቸው፦ ከኤዴሳ ሐዋርያ ከቅዱስ ታዴዎስ (አዳይ)፤ ከቅዱስ ጴጥሮስ ቀጥሎ የሮም የመጀመሪያው ጳጳስ ከሆነው ከቅዱስ ሊኖስ፤ ከቅዱስ ጴጥሮስ ቀጥሎ የአንጾኪያ የመጀመሪያው ጳጳስ ከሆነው ከቅዱስ እዮዲዮስ፤ የቢዛንቲየም የመጀመሪያው ጳጳስ ከሆነው ከቅዱስ ሰንጣክ፤ እንዲሁም የአርል የመጀመሪያው ጳጳስ ከሆነው ከቅዱስ ጥሮፊሞስ።

ምንጮችና ማረጋገጫ

እነዚህ መስመሮች በ2013 እ.ኤ.አ. ጳጳስ ባየርስ ሚመተ ጵጵስና በተቀበሉበት ጊዜ በተበረከተላቸው የሐዋርያዊ ቅብብሎሽ መስመሮች መጽሐፍ ውስጥ የተገኙ ናቸው። እንዲያው ተገልብጠው የቀረቡ አይደሉም። እያንዳንዱ ትስስር በጳጳስ ባየርስ የራሳቸው ምርምር ተመርምሮ ተረጋግጧል፤ ይኸውም በየገጹ በተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት ከተያዙት የጳጳሳት ዝርዝሮችና ከጵጵስና ቅብብሎሽ መደበኛ ታሪካዊ መዛግብት ጋር በማነጻጸር ነው፤ ከእነዚህም መካከል የቅድስት መንበር የሮማ ቅብብሎሽ መዛግብት፣ የቁስጥንጥንያ ኤኩሜኒካል ፓትርያርክ መንበርና የአንጾኪያ ፓትርያርክ መናብርት ዝርዝሮች፣ የሩሲያ ኦርቶዶክስ፣ የብሉይ ካቶሊክ፣ የሶርያ ኦርቶዶክስና የአሦር አብያተ ክርስቲያናት መዛግብት፣ እንዲሁም የእንግሊዝ ጳጳሳትን ሚመት የመዘገበው የዊልያም ስተብስ *Registrum Sacrum Anglicanum* ይገኙበታል።

እነዚህ መዛግብት ከመጽሐፉ በሚለዩበት ቦታ፣ የመዛግብቱ ቃል ተመርጧል፤ መስመሮቹም ታርመዋል። መጽሐፉ የሚያቀርባቸው ነገር ግን ከመዛግብቱ ሊረጋገጡ ያልቻሉ መስመሮች ተትተዋል። በእነዚህ ገጾች ላይ የተጠቀሰውን እያንዳንዱን ጳጳስ አንባቢው በራሱ ቤተ ክርስቲያን መዛግብት ውስጥ ሊያረጋግጥ ይችላል።

የሐዋርያዊ ቅብብሎሽ መስመሮች በአጭሩ

ጳጳስ ባየርስ ከአሥር ሐዋርያት ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ አላቸው፦ ከቀደሙት ከአሥራ ሁለቱ አራቱ፣ ቅዱስ ጳውሎስና ከሰብዓው አምስቱ፤ ይህም በአሥራ አንድ የተለያዩ መንገዶች ሲሆን፣ እያንዳንዱ ከዚህ በታች በራሱ ገጽ ቀርቧል። ቁጥሮቹ በእያንዳንዱ መስመር ያላቸውን ሰፍራ ያሳያሉ።

ሐዋርያት

ሐዋርያ	መንገዶች	ጳጳስ ባየርስ
ቅዱስ ጴጥሮስ	ሮም (ሬቢባ–ብራዚል) · ሮም (ዩትሬክት) · አንጾኪያ (መልካይት) · አንጾኪያ (ኦርቶዶክስ) · አንጾኪያ (የሶርያ ኦርቶዶክስ)	245 · 252 · 169 · 165 · 146
ቅዱስ እንድርያስ	ኪየቭ–ሞስኮ · ቁስጥንጥንያ–አልባኒያ	173 · 264
ቅዱስ ዮሐንስ	ካንተርበሪ · ስኮትላንድ–ሲበሪ	126 · 132
ቅዱስ ቶማስ	የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን	112
ቅዱስ ጳውሎስ	ካንተርበሪ · ስኮትላንድ–ሲበሪ	128 · 134

ከሰብዓው

ከሰብዓው አንዱ	መንገዶች	ጳጳስ ባየርስ
ቅዱስ ታዴዎስ (አዳይ)	የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን	111
ቅዱስ ሊኖስ	ሬቢባ–ብራዚል · ዩትሬክት	244 · 251
ቅዱስ አቮዲዮስ	መልካይት · ኦርቶዶክስ · የሶርያ ኦርቶዶክስ	168 · 164 · 145
ቅዱስ ሰንጣክ	ኪየቭ–ሞስኮ · ቁስጥንጥንያ–አልባኒያ	172 · 263
ቅዱስ ጥሮፊሞስ	ካንተርበሪ · ስኮትላንድ–ሲበሪ	127 · 133

በዚሁ መለኪያ፣ ማለትም በዋናው የሚመት መሰመር፣ የጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እያንዳንዳቸው ወደ አንድ ሐዋርያ የሚደርስ አንድ መሰመር አላቸው። በእያንዳንዱ ሐዋርያ ገጽ ላይ ያለው ሰሌዳ እንደሚመዘግበው፣ ጳጳስ ባየርስ ከእያንዳንዳቸው ጋር አንድ መሰመር ይጋራሉ።

የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፣ በ2026 እ.ኤ.አ.

የቤተ ክርስቲያን መሪ	መሰመሮች	ሐዋርያ	ከጳጳስ ባየርስ ጋር የሚጋራ መሰመር
የሮም ጳጳስ ፓፓ ሊዮ 14ኛ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን	1	ቅዱስ ጴጥሮስ	ሮም (ሁለት መንገዶች)
የሞስኮና የመላው ሩሲያ ፓትርያርክ ኪሪል የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን	1	ቅዱስ ጴጥሮስ (በአንጾኪያ በኩል)	አንጾኪያ፣ በሞስኮ በኩል
የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳሳት ሳራ ሙላሊ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያንና የአንግሊካን ኅብረት	1	አንድ ሐዋርያ፣ በካንተርበሪ በኩል	ካንተርበሪ (ሁለት መንገዶች)
የአንጾኪያ የሶርያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ አግናጥዮስ ኤፍሬም 2ኛ የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን	1	ቅዱስ ጴጥሮስ (በአንጾኪያ በኩል)	አንጾኪያ (የሶርያ ኦርቶዶክስ)
የምሥራቅ ካቶሊኮስ-ፓትርያርክ ማር አዋ 3ኛ የአሦር የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን	1	ቅዱስ ቶማስ	የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን
ጳጳስ ባየርስ	**11**	**አሥር ሐዋርያት**	—

የመሰመሮቹ ብዛት በቅዱስ ሥልጣነ ክህነት ጸጋ ላይ አንዳች አይጨምርም፤ አንድ ሕጋዊ መሰመር ብቻውን በቂ ነውና። እዚህ የቀረቡትም ሊመረምሯቸው ለሚሹ ሰዎች እንደ መዝገብ ሆነው ነው። ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ ውድድር አይደለም፤ ብዙ መሰመሮች ያሉት ጳጳስ፣ እነከን የሌለበትና ሊረጋገጥ የሚችል አንድ መሰመር ብቻ ካለው ጳጳስ የበለጠ ሥልጣንም ሆነ ሕጋዊነት የለውም። በእነዚህ ገጾች ላይ ያለ ምንም ነገር በማንኛውም ጳጳስ ላይ፣ ይልቁንም ሕይወታቸውን በሙሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሰጡት እዚህ በተጠቀሱት ላይ፣ ቅድሚያ እንደ መጠየቅ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። መሰመሮቹ የተመዘገቡት የክርስቲያን ምእመናንና የጳጳስ ባየርስን ክህነት ለመመርመር የሚሻ ማንኛውም ሰው እውነታዎቹን በአንድ ሰፍራ እንዲያገኙ፣ እንዲሁም ትኩረት በሚገባው ሰፍራ፣ በእግዚአብሔር ቃልና በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ላይ እንዲያርፍ ነው።

ቅዱሳንና ሰማዕታት

በእያንዳንዱ ሐዋርያ ገጽ ላይ፣ በመሰመሩ ውስጥ ሰለ እምነት ሕይወታቸውን የሰጡት ሰማዕታት ተብለው ተለይተዋል፤ ቅድሰናቸው የታወጀላቸው ወይም በሌላ መንገድ ለመሠዊያው ክብር የበቁት ደግሞ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ትውፊት፣ በምዕራቡ ትውፊት ወይም በሁለቱም ቅዱሳን ወይም ቡሩካን መሆናቸው ተመልክቷል። አብያተ ክርስቲያናት የትኞቹን ቅዱሳን እንደሚቀበሉና እንድን ሰው በቅድሰና ከማክበራቸው በፊት ምን እንደሚጠይቁ ይለያያሉ፤ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ያሉት ምልክቶች የትኛው ቤተ ክርስቲያን ማንን እንደሚያከብር ያሳያሉ። እነዚህ ምልክቶች የሕይወትን ቅድሰና ብቻ የሚመለከቱ ሲሆኑ በማንኛውም ሚመተ ጽድሰና ትክክለኛነት ላይ ምንም ተጽዕኖ የላቸውም።

✠

የቅብብሎሹን መሰመር ለማየት ሐዋርያ ይምረጡ።

ሐዋርያት



ቅዱስ ጴጥሮስ በሮም (ሬቢባ–ብራዚል)

ሐዋርያና ሰማዕት

ሮም፣ የሬቢባ ቅብብሎሽ፣ ብራዚልና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 245ኛ



ቅዱስ ጴጥሮስ በሮም (ዩትሬክት)

ሐዋርያና ሰማዕት

ሮም፣ ፈረንሳይ፣ ዩትሬክት፣ እንግሊዝና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 252ኛ



ቅዱስ ጴጥሮስ በአንጾኪያ (መልካይት)

ሐዋርያና ሰማዕት

አንጾኪያ፣ የመልካይት ፓትርያርክ መንበር፣ ቤይሩትና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 169ኛ



ቅዱስ ጴጥሮስ በአንጾኪያ (ኦርቶዶክስ)

ሐዋርያና ሰማዕት

አንጾኪያ፣ የኦርቶዶክስ ፓትርያርክ መንበር፣ ሞስኮና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 165ኛ



ቅዱስ ጴጥሮስ በአንጾኪያ (የሶርያ ኦርቶዶክስ)

ሐዋርያና ሰማዕት

አንጾኪያ፣ የሶርያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ መንበር፣ ሕንድና አሜሪካ



ቅዱስ እንድርያስ (ኪየቭ–ሞስኮ)

በመጀመሪያ የተጠራው፣ ሐዋርያና ሰማዕት

ቁስጥንጥንያ፣ ኪየቭ፣ ሞስኮና አሜሪካ



ቅዱስ እንድርያስ (ቁስጥንጥንያ–አልባኒያ)

በመጀመሪያ የተጠራው፣ ሐዋርያና ሰማዕት

ቁስጥንጥንያ፣ አልባኒያና አሜሪካ



ቅዱስ ዮሐንስ (ካንተርበሪ)

ሐዋርያና ወንጌላዊ

ሰምርኔስ፣ ሊዮን፣ ካንተርበሪና አሜሪካ



ቅዱስ ዮሐንስ (ስኮትላንድ–ሲበሪ)

ሐዋርያና ወንጌላዊ

ሰምርኔስ፣ ሊዮን፣ ካንተርበሪ፣ ስኮትላንድና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብሎሹ 132ኛ



ቅዱስ ቶማስ

ሐዋርያና ሰማዕት

የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን፣ ሕንድ፣ እንግሊዝና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብሎሹ 112ኛ



ቅዱስ ጳውሎስ (ካንተርበሪ)

የአሕዛብ ሐዋርያና ሰማዕት

አርል፣ ካንተርበሪ፣ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያንና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብሎሹ 128ኛ



ቅዱስ ጳውሎስ (ስኮትላንድ–ሲበሪ)

የአሕዛብ ሐዋርያና ሰማዕት

አርል፣ ካንተርበሪ፣ ስኮትላንድና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብሎሹ 134ኛ

ከሰብዓው



ቅዱስ ታዴዎስ (አዲይ)

ከሰብዓው አንዱ

የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን፣ ሕንድ፣ እንግሊዝና አሜሪካ



ቅዱስ ሊኖስ (ሬቢባ–ብራዚል)

ከሰብዓው አንዱ

ሮም፣ የሬቢባ ቅብብሎሽ፣ ብራዚልና አሜሪካ



ቅዱስ ሊኖስ (ዩትሬክት)

ከሰብዓው አንዱ

ሮም፣ ፈረንሳይ፣ ዩትሬክት፣ እንግሊዝና አሜሪካ



ቅዱስ አቮዲዮስ (መልካይት)

ከሰብዓው አንዱ

አንጾኪያ፣ የመልካይት ፓትርያርክ መንበር፣ ቤይሩትና አሜሪካ



ቅዱስ አቮዲዮስ (ኦርቶዶክስ)

ከሰብዓው አንዱ

አንጾኪያ፣ የኦርቶዶክስ ፓትርያርክ መንበር፣ ሞስኮና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 164ኛ



ቅዱስ አቮዲዮስ (የሶርያ ኦርቶዶክስ)

ከሰብዓው አንዱ

አንጾኪያ፣ የሶርያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ መንበር፣ ሕንድና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 145ኛ



ቅዱስ ሰንጣክ (ኪየቭ–ሞስኮ)

ከሰብዓው አንዱ

ቁስጥንጥንያ፣ ኪየቭ፣ ሞስኮና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 172ኛ



ቅዱስ ሰንጣክ (ቁስጥንጥንያ–አልባኒያ)

ከሰብዓው አንዱ

ቁስጥንጥንያ፣ አልባኒያና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 263ኛ



ቅዱስ ጥሮፊሞስ (ካንተርበሪ)

ከሰብዓው አንዱ

አርል፣ ካንተርበሪ፣ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያንና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 127ኛ



ቅዱስ ጥሮፊሞስ (ስኮትላንድ–ሲበሪ)

ከሰብዓው አንዱ

አርል፣ ካንተርበሪ፣ ስኮትላንድና አሜሪካ

ጳጳስ ባየርስ፣ በቅብብሎሹ 133ኛ



Amharic Scripture quotations: copyright © 1962, 2003 United Bible Societies. Revised Amharic Bible in XML (2003). Printed version by United Bible Societies (C)1962. E-Text in transliterated ASCII format by Lapsley/Brooks Foundation 1994. Unicode UTF-8 transformation and XML-tagging by Dirk Röckmann 2003 (www.nt-text.net). With kind permission of the Bible Society of Ethiopia. Every non-commercial work using this data in any form must fully include this copyright statement! Every commercial use of parts or the complete data in any form needs written permission of the Bible Society of Ethiopia!

ቅዱሳት ሥዕላት፦ ቅ. ጴጥሮስ፣ የሲና ተራራ፣ 6ኛው ክፍለ ዘመን፣ የሕዝብ ንብረት (public domain)። ቅ. ጴጥሮስ (ዩትሬክት)፣ በሉካስ ቮርስተርማን 2ኛ የተሠራ የቅርጽ ሕትመት፣ 1660 እ.ኤ.አ.፣ Rijksmuseum፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ጴጥሮስ በአንጾኪያ (መልካይት)፣ የብሥራት ካቴድራል፣ ሞሰኮ፣ እ.ኤ.አ. በ1399 ገደማ፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ጴጥሮስ በአንጾኪያ (ኦርቶዶክስ)፣ የቅድስት ሶፍያ ካቴድራል፣ ኖቭጎሮድ፣ እ.ኤ.አ. በ1050 ገደማ፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. እንድርያስ፣ Walters Art Museum፣ ባልቲሞር፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ዮሐንስ፣ ፍጥሞ፣ እ.ኤ.አ. በ1500 ገደማ፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ቶማስ፣ 14ኛው ክፍለ ዘመን፣ ፎቶግራፍ፦ Herbert Frank፣ CC BY 2.0። ቅ. ጳውሎስ፣ St. Paul’s Episcopal Church፣ ሲያትል፣ ፎቶግራፍ፦ Joe Mabel፣ CC BY-SA 3.0። ቅ. ታዴዎስ፣ የሲና ተራራ፣ 10ኛው ክፍለ ዘመን፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ስንጣክ፣ ላጉዴራ፣ ቆጵሮስ፣ 1192 እ.ኤ.አ.፣ ፎቶግራፍ፦ Dumbarton Oaks፣ CC0። ቅ. ሊኖስ፣ የሩሲያው «የቅዱሳን ገድል»፣ 1903-1911 እ.ኤ.አ.፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ሊኖስ (ዩትሬክት)፣ ሕትመት፣ Rijksmuseum፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ጥሮፊሞስ፣ በአርል የሚገኘው የቅዱስ ጥሮፊሞስ ገዳም

አደባባይ፣ 12ኛው ክፍለ ዘመን፣ ፎቶግራፉ ለሕዝብ ንብረትነት የተለቀቀ። ቅ. አቮዲዮስ (መልካይት)፣ የኢጣሊያ የሥዕል ትምህርት ቤት፣ 17ኛው ክፍለ ዘመን፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. አቮዲዮስ (ኦርቶዶክስ)፣ የሩሲያው «የቅዱሳን ገድል»፣ 1903-1911 እ.ኤ.አ.፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ጴጥሮስ በአንጾኪያ (የሶርያ ኦርቶዶክስ)፣ የራቡላ ወንጌል፣ 586 እ.ኤ.አ.፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. እንድርያሰና ቅ. ሰንጣክ (ቁሰጥንጥንያ–አልባኒያ)፣ የባስልዮሰ 2ኛ ሜኖሎጊዮን፣ እ.ኤ.አ. በ1000 ገደማ፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ጳውሎሰ (ሰኮትላንድ–ሲበሪ)፣ የሰፓዮ-ፕሪኦብራዠንስኪ ገዳም፣ ያሮስላቭል፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ዮሐንስ (ሰኮትላንድ–ሲበሪ)፣ የኬልሰ መጽሐፍ፣ እ.ኤ.አ. በ800 ገደማ፣ የሕዝብ ንብረት። ቅ. ጥሮፊሞስ (ሰኮትላንድ–ሲበሪ)፣ የሩሲያው «የቅዱሳን ገድል»፣ 1903-1911 እ.ኤ.አ.፣ የሕዝብ ንብረት። ሁሉም ምስሎች ከWikimedia Commons የተገኙ ናቸው፤ ተቆርጠው መጠናቸው ተቀይሯል። ሙሉ የምንጭ መግለጫዎች በእያንዳንዱ ሐዋርያ ገጽ ላይ ይገኛሉ።